# የቡና ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ የዳይሬክተሮች ቦርድ
# አባላት ጥቆማ እና ምርጫ አፈፃፀም የአሰራር ደንብ

አዲስ አበባ

2010 ዓ.ም

1. መግቢያ .......... 1
2. ርዕስ .......... 2
3. ትርጓሜ .......... 2
4. የአስመራጭ ኮሚቴ መቋቋም .......... 2
5. የአስመራጭ ኮሚቴ አባልነት መስፈርት እና ስብጥር .......... 3
6. የዳይሬክተሮች ቦርድ ተግባራትና ኃላፊነቶች .......... 3
7. የአስመራጭ ኮሚቴው ተግባራትና ኃላፊነቶች .......... 4
8. የአስመራጭ ኮሚቴ ደንቦች እና አሠራሮች .......... 4
9. የቦርድ አባላት እጩዎች ጥቆማ ሂደት .......... 5
10. የዳይሬክተሮች ቦርድ የምርጫ ሂደት .......... 8
11. የድምፅ አሰጣጥ ሂደት .......... 8
12. ይህ የአሠራር ደንብ ተፈፃሚ ስለማይሆንበት ሁኔታ .......... 10
13. የመመሪያ ዝግጅት .......... 10
14. የሌሎች ሕግጋት ተፈፃሚነት .......... 10
15. ስለማሻሻል .......... 10
16. የሚፀናበት ቀን .......... 10

1. <u>መግቢያ</u>

በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ ቁጥር 350መሰረት የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ በአክስዮን ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ እንደሚመረጡ ይደነግጋል፡፡ ይህንን ሕግ መሰረት አድርጎ የተቋቋመው ቡና ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማህበር በመተዳደሪያው ደንብ አንቀጽ 7.1(ሐ) ላይ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን የመምረጥና የመሾም ስልጣን የባለአክሲዮኖች መሆኑንና ይህም በጠቅላላ ጉባኤ ተግባራዊ እንደሚደረግ በግልጽ አስቀምጧል፡፡

የአንድ አክስዮን ማህበር መልካም አስተዳደር ከሚገለጽባቸው መንገዶች መካከል የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ ሂደት ግልፅነት የተላበሰ እንዲሆን ማስቻል ሲሆን፣ ይህንን እውን ለማድረግ በዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት የሚያገለግሉ ብቁ የሆኑ እና ተገቢ እጩዎችን የሚያቀርብ አስመራጭ ኮሚቴ በጠቅላላ ጉባኤ መቋቋም እንዳለበት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው የባንክ መልካም አስተዳደር[Bank Corporate Governace] መመሪያ ቁጥር SBB/62/2015 አንቀጽ 6 ላይ ከመደንገጉም በተጨማሪ ይሄው ጠቅላላ ጉባኤ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ እና ምርጫ አፈፃፀም የአሰራር ደንብን ማጽደቅ እንዳለበትም ይገልጻል፡፡ ለዚህም ይረዳ ዘንድ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አንድ ሞዴል መመሪያ በማዘጋጀት በሀገሪቱ ውስጥ በሥራ ላይ ላሉት ባንኮችና ኢንሹራንስ ኩባንያዎች ልኳል፡፡

ከዚህ ሞዴል መመሪያ በመነሳትና በባንካችን ውስጥ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣ የባንኩን ጥቅሞች ከሁሉ በተሻለ ለማስጠበቅ፣ የባንኩን ሥራ አመራር የሚመሩ እና የሚቆጣጠሩ፣ ለዚህም ሐቀኛ የመሪነት ክህሎት እና ብቃት ያላቸውን እጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ለማቅረብ እንዲረዳ በማሰብ ይህ የአሰራር ደንብ ተዘጋጅቷል፡፡

ስለሆነም የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ በምን መልኩ እንደሚቋቋም ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ስብሰባ እንደ መመሪያ እንዲያገለግል እና አስመራጭ ኮሚቴውም እጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን በማቅረቡ እና በማስመረጡ ሂደት ሊከተላቸው የሚገቡ አሰራሮችን ለመደንገግ ይህ የአሰራር ደንብ ወጥቷል፡፡

2. <u>ርዕስ</u>

ይህ የአሰራር ደንብ “የቡና ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማህበር የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና የምርጫ አፈጻጸም የአሰራር ደንብ” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ በሌላ አኳኋን ካልተተረጐመ በስተቀር፣ በዚህ የአሰራር ደንብ ውስጥ ያሉት ቃላት ከዚህ በታች የተሰጣቸውን ትርጓሜዎች ይይዛሉ፡-

3.1 “ቦርድ” ማለት የቡና ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ የዳይሬክተሮች ቦርድ ነው፡፡

3.2 “ፕሬዚዳንት” ማለት የቡና ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ ፕሬዚዳንት [ዋና ሥራ አስፈጻሚ] ሲሆን የባንኩን የዕለት ተዕለት ሥራዎች በዋና ኃላፊነት የመምራት ስልጣን የተሰጠው ሰው ነው፡፡

3.3 “ዳይሬክተር” ማለት የቡና ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ ማናቸውም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ነው፡፡

3.4 “ሰራተኛ” ማለት በቡና ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ የተሾመ ወይም የተቀጠረ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ፤ ወይም ሌላ ማናቸውም ሰው ሆኖ የዕለት ተዕለት ሥራዎችን የሚያከናውን ነው፡፡

3.5 “ጠቅላላ ጉባዔ” ማለት የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ማለት ነው፡፡

3.6 “ተጽእኖ ፈጣሪ ባለአክሲዮን” ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከጠቅላላው የቡና ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ የተከፈለ ካፒታል ውስጥ 2% ወይም ከዚያ በላይ ድርሻ የያዘ ሰው ማለት ነው፣

3.7 “ተጽእኖ ፈጣሪ ያልሆነ ባለአክስዮን” ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከጠቅላላው የቡና ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ የተከፈለ ካፒታል ውስጥ ከ2% በታች የአክሲዮን ድርሻ የያዘ ሰው ማለት ነው፡፡

3.8 “አስመራጭ ኮሚቴ” ወይም “ኮሚቴ” ማለት የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ ነው፡፡

4. <u>የአስመራጭ ኮሚቴ መቋቋም</u>

4.1 የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በሥራ ላይ ያለው ቦርድ የሥራ ጊዜው ከመጠናቀቁ አንድ ዓመት አስቀድሞ አስመራጭ ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡

4.2 የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ብዛት 5 ይሆናል፡፡

4.3 ጠቅላላ ጉባኤው የአስመራጭ ኮሚቴውን የመምረጥና ከሚቴው የሚመራበትን የአሰራር ደንብ የማፅደቅ ኃላፊነት አለበት፡፡

4.4 ጠቅላላ ጉባኤው ለአስመራጭ ኮሚቴነት የሚመረጡ 15 እጩዎችን በመጠቆም ለእያንዳንዱ እጩ በተሰጠው ድምፅ መሠረት ከእነርሱ መካከል ከፍተኛ ድምፅ ያገኙ 5 የሚሆኑትን በመቀበል ያፀድቃል፡፡

4.5 ጠቅላላ ጉባኤው ባለአክስዮኖች ባላቸው አክስዮን መጠን ልክ በምስጢራዊ ድምፅ አሰጣጥ ስርዓት አስመራጭ ኮሚቴውን ይመርጣል፡፡

4.6 የአስመራጭ ኮሚቴው ምርጫ ውጤት በዚያው ቀን ይገለፃል፡፡

5. <u>**የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት የሚመረጡበት መስፈርት**</u>

5.1 የአስመራጭ ኮሚቴው አባላት የሚከተሉትን ማሟላት አለባቸው፡-

ሀ) ባለአክሲዮኖች ሊሆኑ ይገባል፣

ለ) በአስመራጭ ኮሚቴ አባልነት ለመስራት ፍላጐት ሊኖራቸው ይገባል፣

ሐ) የባንኩ ተቀጣሪ ሊሆኑ አይገባም፣

መ) ቢያንስ የ10ኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቁ መሆን አለባቸው፡፡

5.2 ጠቅላላ ጉባዔው የአስመራጭ ኮሚቴውን በሚመርጥበት ወቅት ከእነርሱ መካከል ቢያንስ 2 አባላት ተጽእኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክስዮኖች መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

5.3 የቦርድ አባላት የአስመራጭ ኮሚቴ አባል ሆነው ሊመረጡ አይችሉም፡፡

5.4 አስመራጭ ኮሚቴው ከአባላት መካከል ሊቀመንበር ይመርጣል፡፡

5.5 አስመራጭ ኮሚቴው የኮሚቴው አባል ያልሆነ እና ድምፅ የመስጠት መብት የሌለው ፀሐፊ ሊመድብ ይችላል፡፡

6. <u>**የዳይሬክተሮች ቦርድ ተግባራትና ኃላፊነቶች**</u>

**ቦርዱ፡-**

6.1 የአስመራጭ ኮሚቴን የምርጫ ሂደት የማስፈፀም ኃላፊነት አለበት፣

6.2 የአስመራጭ ኮሚቴው የምርጫ ጉዳይ በጠቅላላ ስብሰባው አጀንዳ ውስጥ እንዲካተት ያደርጋል፣

6.3 ለአስመራጭ ኮሚቴው የማቴሪያል እና የፋይናንስ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

7. **<u>የአስመራጭ ኮሚቴው ተግባራትና ኃላፊነቶች</u>**

7.1 የአስመራጭ ኮሚቴው ምርጫ በተጠናቀቀ በ1 ወር ጊዜ ውስጥ ስብሰባ ጠርቶ የኮሚቴውን ሰብሳቢ እና ፀሐፊ መምረጥ አለበት፣

7.2 የአስመራጭ ኮሚቴው እጩ የቦርድ ተወዳዳሪዎችን የመቀበልና ለጠቅላላ ጉባኤ አስቀርቦ የማስመረጥ ኃላፊነት አለበት፣

7.3 የቦርድ አባላት በእጩነት የማቅረብ እና የማስመረጥ ሂደት አግባብነት ባላቸው የአገሪቱ ሕጎችና በዚህ የአሰራር ደንብ መሰረት በግልፅነት፤ በፍትሐዊነት እና በታማኝነት መከናወኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

8. **<u>የአስመራጭ ኮሚቴ ደንብና  አሠራር</u>**

8.1 አስመራጭ ኮሚቴው መደበኛ ስብሰባ የሚያከናወንበትን ቀን፤ሰዓት እና ቦታ ይወስናል፡፡

8.2 የአስመራጭ ኮሚቴው ሰብሳቢ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

8.3 ከአስመራጭ ኮሚቴ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ሲገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሟላል፡፡

8.4 የአስመራጭ ኮሚቴው ውሳኔዎች የሚተላለፉት ከግማሽ በላይ በሚሆኑ አባላቱ ድጋፍ ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን የውሳኔ ሐሳቦች እኩል ድምፅ የተሰጠ እንደሆነ ሰብሳቢው የደገፉት የውሳኔ ሐሳብ የኮሚቴው ውሳኔ ሆኖ ያልፋል፣

8.5 የኮሚቴው ሰብሳቢ ኮሚቴውን የመምራት ኃላፊነት አለበት፡፡ በዚሁ መሰረት ስብሰባዎችን የመጥራትና አጀንዳዎችን ማዘጋጀት እንዲሁም ኮሚቴውን በመወከል ግንኙነት የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡ የኮሚቴው ፀሐፊ የሁሉንም ውሳኔዎች እና የስብሰባ ሂደት ቃለጉባዔ የመያዝ ኃላፊነት አለበት፡፡

8.6 የስብሰባዎች ቃለጉባዔዎች ተይዘው፤ ቁጥር ተሰጥቷቸው በሁሉም ተሳታፊ አባላት ሊፈረምባቸው ይገባል፡፡

8.7 ከአስመራጭ ኮሚቴ አባላት መካከል ከ50% (ሃምሳ በመቶ) በታች የሚሆኑት በዚህ ደንብ በተጠቀሰው አኳኋን የሹመት ጊዜያቸውን ከማጠናቀቃቸው በፊት የለቀቁ እንደሆነ ቀሪዎቹ አባላት ኮሚቴው በተቋቋመበት ወቅት በተሰጣቸው ድምፅ ብዛት

ቅደም ተከተል በተጠባባቂነት ከተያዙት አባላት መካከል ሊሾሙ ይችላሉ፡፡ ይህንኑ ሁኔታም ለቦርዱ ያሳውቃሉ፡፡

8.8 ቀሪዎቹ የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ከ50% (ሃምሳ በመቶ)በታች የሆኑ እንደሆነ ከተጠባባቂ አባላት መካከል የመሾማቸው ነገር ቀርቶ ሁኔታውን ለቦርዱ በማሳወቅ ሥራቸውን ማቆም አለባቸው፣

8.9 አስመራጭ ኮሚቴው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 8.8 መሠረት ሥራውን ካቋረጠ፣ ቦርዱ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት የማስመረጥ ሂደቱን ይረከባል፡፡ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሰረት ጠቅላላ ጉባኤው ዳይሬክተሮቹን ይሾማል፡፡

9. <u>የቦርድ አባላት እጩዎች ጥቆማ ሂደት</u>

9.1 አስመራጭ ኮሚቴው ሰፊ ሽፋን ባላቸው የሕትመት እና የኤሌክትሮኒክ ሚዲያዎች (በቴሌቪዥን፣በሬድዮ እና በባንኩ ድረገጽ) አማካኝነት እጩዎችን የማቅረብ ሂደት መጀመሩን ማሳወቅ እና ባለአክሲዮኖች ብቃት ያላቸውን እጩዎች እንዲጠቁሙ መጋበዝ አለበት፡፡

9.2 አስመራጭ ኮሚቴው በእጩዎች መሟላት ያለባቸውን አነስተኛ መስፈርቶች በማስታወቂያው ውስጥ ማካተት እና የጥቆማው ሂደት በምን መልኩ እንደሚካሄድ መግለጽ አለበት፡፡

9.3 አስመራጭ ኮሚቴው ተገቢ ነው ብሎ በሚያስበው መልኩ እጩዎችን የመጠቆሙ ሂደት መቼ እንደሚያበቃ ይወስናል፡፡ ሆኖም ግን እጩዎችን ለመጠቆም የሚሰጠው ጊዜ ከ3 ወራት በታች ሊሆን አይችልም፡፡

9.4 የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ለቦርድ አባልነት ሊጠቆሙ አይችሉም፡፡አስመራጭ ኮሚቴው ያሉበትን ግዴታዎች ለመወጣት የሚያስችሉ ሰራተኞች በመያዝ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ያቋቁማል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ኮሚቴው ለእጩዎች ምዝገባ የሚያገለግል መዝገብ ያዘጋጃል፡፡

9.5 አስመራጭ ኮሚቴው ለእያንዳንዱ ባለአክሲዮን ምቹ በሆነ የግንኙነት ዘዴ እጩውን የሚጠቁምበትን ዕድል ማመቻቸት አለበት፡፡ ይህም መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ከሚካሔድበት ቀን ሁለት ወራት አስቀድሞ መሆን አለበት፡፡

9.6 አስመራጭ ኮሚቴው ከዚህ የሚከተሉትን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡-

ሀ)ተጽእኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክስዮኖች ከጠቅላላው የተከፈለ ካፒታልመካከል ቢያንስ 30 በመቶ የሚሆነውን በባለቤትነት የያዙ እንደሆነ ለቦርድ አባልነት እጩ ሆነው ከሚቀርቡት አባላት መካከል 1/3ኛ (አንድ ሶስተኛ) የሚሆኑት የሚጠቆሙት ተጽእኖ ፈጣሪ ባልሆኑ ባለአክሲዮኖች ብቻ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

ለ) ተጽእኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክስዮኖች ከጠቅላላው የተከፈለ ካፒታል መካከል ከ30 በመቶ በታች የሚሆነውን የያዙ እንደሆነ ለቦርድ አባልነት ከሚቀርቡት እጩዎች መካከል ¼ኛ (አንድ አራተኛ) የሚሆኑትን የሚጠቁሙት ተጽእኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክስዮኖች ብቻ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ እና

ሐ) ቀሪዎቹ 2/3ኛ ወይም ¾ኛ እጩዎች እንደ አግባብነቱ በሁሉም ባለአክሲዮኖች መጠቆማቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

9.7 በዚህ አንቀጽ ከላይ በንዑስ አንቀጽ 9.6 የተገለፀውን ንፅፅር ለማረጋገጥ፣ አስመራጭ ኮሚቴው ከእጩዎቹ መካከል 2/3ኛ ወይም ¾ኛ የሚሆኑትን በሁሉም ተሳታፊ ባለአክሲዮኖች ድምፅ በማስመረጥ እንደ አግባብነቱ ቀሪዎቹን 1/3ኛ ወይም 1/4ኛ እጩዎች በመለስተኛ አክሲዮኖች/ተጽእኖ ፈጣሪ/ተደማጭነት ያለው ባለአክሲዮን" ባልሆኑ ባለአክስዮኖች በተሰጡ ድምፆች ብቻ ያስመርጣል፡፡

9.8 ባለአክሲዮኖች ጥቆማ በሚያካሂድበት ሂደት በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 9.7 የተገለፀው ንፅፅር ሊሟላ ካልቻለ፣ አስመራጭ ኮሚቴው ንፅፅሩን የማስተካከል እና የማስጠበቅ ኃላፊነት አለበት፡፡ እነዚህ ንፅፅሮች መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ፣ ኮሚቴው እንደ አግባብነቱ 2/3ኛ ወይም ¾ኛ የሚሆኑት እጩዎች ከመጠቆማቸው በፊት የእጩዎቹን 1/3ኛ ወይም ¼ኛ ድምፅ አሰጣጥ ያካሂዳል፡፡

9.9 በእጩነት የሚቀርቡት ሰዎች ብዛት የባንኩን ጠቅላላ የቦርድ አባላት ብዛት 12 (አስራ ሁለት) ሁለት እጥፍ ማለትም 24 (ሃያ አራት)ይሆናል፡፡ ኮሚቴው ፈቃደኛ ያልሆኑ እጩዎችን ለመተካት 12 (አስራ ሁለት) ተጠባባቂ እጩዎችን ዝርዝር ይይዛል፡፡

9.10 ለቦርድ አባልነት እጩዎች የሚቀርቡት በሚያገኙት ድምፅ (የተከፈሉ አክሲዮኖች ብዛት) መሠረት ይሆናል፡፡ ከአንድ በላይ የሆኑ እጩዎች እኩል

ድምፅ ያገኙ እንደሆነ አስመራጭ ኮሚቴው ከሁለቱ በትምህርት ደረጃ፣ በልምድ እና ተገቢ ነው ብሎ በሚያስበው ሌላ መስፈርት ይመርጣል፡፡

9.11 አስመራጭ ኮሚቴው ለቦርድ አባልነት ከቀረቡት እጩዎች መካከል አጥጋቢ የሆኑትን ዝርዝር ይይዛል፡፡ በማስከተል

ሀ) በባንኩ ወይም በእርሱ ቅርንጫፎች እና ንዑሳን ቅርንጫፎች ሁሉም ሰው ሊያይ በሚችልባቸው ስፍራዎች ዝርዝሩን ይለጥፋል፣

ለ) ከፍተኛ ስርጭት ባላቸው ጋዜጦች ያሳትማል፣ እንዲሁም

ሐ) በባንኩ ድረገጽ ላይ ያወጣል፡፡ እንደ አስፈላጊነቱም ለባለአክሲዮኖች በአጭር የፅሑፍ መልዕክት ይልካል፡፡ እነዚህ ተግባራር የሚፈፀሙትምርጫውን ለማካሄድ መደበኛ የጠቅላላ የባለአክሲዮኖች ስብሰባ ከሚካሄድበት ቀን ቢያንስ 1 ወር ቀደም ብሎ ይሆናል፡፡

9.12 አስመራጭ ኮሚቴው ስለ እያንዳንዱ እጩ ቢያንስ ቢያንስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ያካተተ መረጃ በማካተት ለጠቅላላ ጉባዔው ያቀርባል፡-

ሀ) ስም እና እድሜ

ለ) ያገኛቸው ድምፆች ብዛት

ሐ) የትምህርት ደረጃ

መ) የሥራ ልምድ

ሠ) በቦርዱ እና በሌሎች መስሪያ ቤቶች ያለው ወቅታዊ አባልነት

9.13 የአስመራጭ ኮሚቴው የውሳኔ ሐሳብ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች እና አግባብነት ባላቸው ሕግጋት ስለ ዳይሬክተሮች ቦርድ ስብጥር የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡

9.14 በእጩነት የቀረቡት ሰዎች ብዛት በዚህ የአሰራር ደንብ ከተቀመጠው ቁጥር በታች ከሆነ ወይም በእጩነት የቀረቡት ሰዎች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተቀመጡትን መስፈርቶች የማያሟሉ ከሆኑ አስመራጭ ኮሚቴው የእጩዎቹ ብዛት መስፈርቱን የሚያሟላ እንዲሆን የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል፤ በቂ የእጩዎች ብዛት ሊገኝ የማይችል ከሆነ ኮሚቴው ይህንኑ ለጠቅላላ ስብሰባው በማሳወቅ ስብሰባው ምርጫውን እንዲያካሂድ ያደርጋል፡፡

## 10. የዳይሬክተሮች ቦርድ የምርጫ ሂደት

10.1 አስመራጭ ኮሚቴው ከጠቅላላ ጉባዔው ፀሐፊ ጋር በመተባበር የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫን ሂደት የማካሄድ ኃላፊነት አለበት፡፡

10.2 አስመራጭ ኮሚቴው የእጩዎቹን ዝርዝር ከመረጃዎቻቸው ጋር ለጠቅላላው ጉባዔው ያቀርባል፣

10.3 አስመራጭ ኮሚቴው በስብሰባው ወቅት እጩዎች ለጠቅላላው ጉባዔ እራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ እና በቦርድ አባልነት ለመሥራት ያላቸውን ፍላጐት እንዲገልፁ እድል ይሰጣል፡፡

10.4 አስመራጭ ኮሚቴው ከባንኩ የሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ባለአክሲዮኖች ድምፅ የሚሰጡባቸውን ድምፅ መስጫዎች እና የድምፅ ሳጥኖች ያዘጋጃል፡፡

10.5 ድምፅ መስጫው ቢያንስ ከዚህ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

ሀ) የባለአክሲዮኑን ስም፣

ለ) በባለአክሲዮኑ የተያዙ አክሲዮኖች ብዛት፣

ሐ)የስብሰባው ልዩ መለያ ቁጥር፣

መ) የባንኩ ስም እና አርማ፣

ሠ) የባንኩ ማህተም፤ እና

ረ) ባለአክሲዮኑ ሊመርጣቸው የሚፈልጋቸውን እጩዎች ስም የሚፅፍበት ስፍራ፡፡

10.6 ድምፅ መስጫዎቹ ባለአክሲዮኖች በጉባዔው ስለመገኘታቸው እንዲፈርሙ በሚደረግበት ወቅት ይሰራጫል፡፡

10.7 ከእጩዎቹ መካከል ማንኛውም ሰው በቦርድ አባልነት ለመመረጥ ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም በሌላ ምክንያት ተቀባይነት ካላገኘ፣ ቀጣዩ በተጠባባቂነት የተያዘው እጩ ተተክቶ ተመሳሳይ አሠራር ሥራ ላይ ይውላል፡፡

## 11.የድምፅ አሰጣጥ ሂደት

11.1 አስመራጭ ኮሚቴው ለምርጫው አግባብነት አለው ብሎ በሚያስበው መልኩ ድምፅ መስጫ ሳጥኖችን ያዘጋጃል፣

11.2 ባለአክሲዮኖች በድምፅ መስጫዎቹ ላይ ሊመርጧቸው የሚፈልጓቸውን እጩዎች ስሞች በመፃፍ ለምርጫው በተዘጋጁት ሳጥኖች ውስጥ ያስገባሉ፡፡

11.3 ባለአክሲዮኖች በግል ወይም በተወካያቸው አማካኝነት ድምፅ የሚሰጡበት ሁኔታ በባንኩ መመስረቻ ጽሑፍ እና መተዳደሪያ ደንብ ላይ እንደተገለፀው ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን አንድ ባለአክሲዮን የራሱን አክሲዮን አካትቶ ከጠቅላላው የተከፈለካፒታል ከ10 (ከአስር በመቶ)በላይ የሚሆነውን አክሲዮን በባለቤትነት የያዙ ባለአክሲዮኖችን ወክሎ ድምፅ መስጠት አይችልም፡፡

11.4 የድምፅ አሰጣጡ ሂደት ከተጠናቀቀ በኋላ አስመራጭ ኮሚቴው ከፀሐፊው እና ከድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ጋር በመተባበር ድምፆቹን ይቆጥራል፡፡

11.5 አስመራጭ ኮሚቴው በእያንዳንዱ እጩ የተሰጠውን ድምፅ ብዛት እና ውድቅ የሚደረጉ የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ብዛት ይመዘግባል፡፡ አንዳንዶቹ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ውድቅ የተደረጉበትን ምክንያት በወረቀቱ በራሱ ላይ በግልፅ በመፃፍ በአስመራጭ ኮሚቴ ተረጋግጦ ይፈረምበታል፡፡

11.6 አንድ ድምፅ መስጫ ወረቀት ውድቅ የሚደረገው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ሁኔታዎች ይሆናል፡-

ሀ) ድምፅ መስጫው ወረቀት የባለአክሲዮኑን ስም ያልያዘ ከሆነ፣

ለ) ድምፅ መስጫው ወረቀት ባለአክሲዮኑ በባለቤትነት የያዛቸውን አክሲዮኖች ብዛት የማይገልፅ ከሆነ፣

ሐ) ድምፅ መስጫው ወረቀት የባንኩን ስም እና አርማ ካልያዘ፣

መ) ድምፅ መስጫው ወረቀት የእጩው ስም ካልተፃፈበት፣

ሠ) ድምፅ መስጫው ወረቀት ፊርማ ከሌለበት፣

ረ) ድምፅ መስጫው ወረቀት ስርዝ ድልዝ ካለበት፣

ሰ) ድምፅ መስጫው ወረቀት የባለአክሲዮኑን መለያ ቁጥር ካልያዘ፣

11.7 የድምፅ ቆጠራው ሂደት ከተጠናቀቀ በኋላ አስመራጭ ኮሚቴው የድምፅ አሰጣጡንና የቆጠራውን ሂደት እንዲሁም የውጤቶቹን ተቀባይነት በተያዘው ቃለጉባዔ እና ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀው ቅጽ ላይ በመፈረም ያረጋግጣል፣

11.8 የተቆጠሩት ድምፆች ታሽገው ለብቻ ይያዛሉ፣

11.9 የድምፅ ቆጠራው ውጤት በዚያው ቀን ለጠቅላላው ስብሰባ ይገለፃል፤ ይህ የማይቻል ከሆነ ውጤቱ በቀጣዩ የሥራ ቀን በባንኩ ዋናው መ/ቤት የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ይለጠፋል፣

## 12. ይህ የአሠራር ደንብ ተፈፃሚ ስለማይሆንበት ሁኔታ

12.1 ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲያጋጥሟቸው ይህ የአሰራር ደንብ ተፈፃሚ አይሆንም፡-

ሀ) በጠቅላላ የባለአክሲዮኖች ስብሰባ ወይም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የአገልግሎት ጊዜያቸው ከማብቃቱ በፊት ከቦርድ አባልነት ሲነሱ፣

ለ) ከቦርድ አባልነታቸው በፈቃዳቸው ሲለቁ፣

ሐ) በማናቸውም ምክንያት በቦርዱ አባልነት መቀጠል የማይችሉ ከሆነ ወይም

መ/ አስመራጭ ኮሚቴው ያቀረባቸውን እጩዎች ከ50 በመቶ በላይ በሆኑ ድምፆች ተቀባይነት ሲያጡ፣

12.2 ከላይ በቁጥር 12.1 ከተገለፁት ሁኔታዎች ማናቸውም ከተከሰተ የቦርድ አባላት ምርጫ የሚካሄደው በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ መሠረት ይሆናል፡፡

12.3 ከቦርድ አባላት መካከል ከ50 በመቶ በታች የሆኑት አባላት የአገልግሎት ጊዜያቸው ከማብቃቱ በፊት ከአባልነት የለቀቁ እንደሆነ የኢትዮጵያ ንግድ ሕግ አንቀጽ 351 ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## 13. የመመሪያ ዝግጅት

አስመራጭ ኮሚቴው ይህንን የአሰራር ደንብ ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ ዝርዝር መመሪያ ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡

## 14. የሌሎች ሕግጋት ተፈፃሚነት

ይህንን የአሠራር ደንብ ተፈፃሚ ለማድረግ ሌሎች ተፈፃሚነት ያላቸው ሕግጋት እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ አግባብነት ይኖራቸዋል፡፡

## 15. ስለማሻሻል

ይህ የአሰራር ደንብ በጠቅላላ ጉባዔው ሲፈቀድ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 16. የሚፀናበት ቀን

ይህ የአሰራር ደንብ በጠቅላላ ጉባዔው ከፀደቀበት ቀን አንስቶ የፀና ይሆናል፡፡